ለውድ ወንድሜ አቶ ጌታቸው ረዳ በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታዬ ባሉበት ይድረስዎ። ለደብዳቤዎ አስቸኳይ መልስ ባለመስጠቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

እኔም ትግሬ ነኝ በሚል ርዕስ በፃፍኩት ላይ የተነሳውን ተቃውሞ አንብቤዋለሁ ፣ አዳምጬዋለሁም። በእውነቱ ከሆነ የተሰጠው መልስ የተለያየ ቢሆንም ብዙዎቹ እኔ የጻፍኩትን ለመረዳት ሳይሞክሩ እራሳቸው የሚያስቡትን ነው እንደ ተቃውሞ ያቀረቡት። የቀረቡትን ሃሳቦች ሁሉንም በአንድ ዓይን ማየት አይቻልም። ገንቢ የሆኑ በመካከላቸው ሲኖሩ አውቆ በማጣመም ያልፃፍኩትን ለመተርጎም የሞከሩም አሉ።አንዳንዶቹ በግል አጀንዳቸው ዙሪያ የተመሰረተ የፖለቲካ ድርጅታቸውን ጥቅም ብቻ በሚመለከት ታላቅ ሃላፊነት የተሞላበትን ሥራ ወደ ጎን በማድረግ ነገ በኢትዮጵያ ህልውና ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ችግር ባለመመልከት ለዛሬ ብቻ በማሰብ የአቀረብኩትን ክቡር አሳብ ሲያጣጥሉት እንደነበር ለእርሶ ድብቅ አደለም።

አሁን በየፓልቶኩ ክፍል የምንሰማው የጅምላ ውንጀላ እንዲፈጠር ምክንያት የሆኑት ወያኔና ወያኔን በጭፍን የሚደግፉ የትግራይ ልጆችም በቀጥታ ተጠያቂዎች ናቸው።እነዚህ በውጭ አገር ተቀምጠው የአገራቱ ደም በወያኔ በተዘረጋው የዘረኝነታ መረብ እየጠመዱ ያሉ የትግራይ ተወላጆች አማራው ሲጨፈጨፍ ፣ ኦሮሞዎች ሲጋዙ ምንም አይነት ተቃውሞ ባለማሳየታቸውና እንዲያውም ጭፍን ድጋፍ ለወያኔ ሲሰጡ ፣ በተለይም በግንቦቱ ምርጫ ምክንያት የተደረገውን ጭፍጨፋ ለማውገዝ አለመፈለጋቸው እና ሌሎች ብዙ ክስተቶች ተደራርበው ግፍ እየደረሰበት ባለ ሕዝብ ቢጠሉ የሚደነቅ አይሆንም።ቢሆንም ግን እነዚህ የጥቅም ተካፋይ የሆኑ ባንዳዎች የትግራይን ሕዝብ እንደሚወክሉ እየተደረገ የትግራይን ደሃ ሕዝብ አብሮ በጥፋተኝነት በዘረኝነት መፈረጅ ነገ በታሪክ ተጠያቂ የሚያደረግ ነው ብዬ አምናለሁ።

በተለይ በ ኢ. ኢ. ዲ. ኤን ( በኢሜል በሚደረግ ግኑኝነት) ላይ ሁኔታውን በማጋጋል ይፅፉ የነበሩት ግለሰብ የፃፉት ደርሶኝ ስመለከተው በጣም ተገርሚለሁ። እሳቸው VEDR ብለው ባቋቋሙት የፓልቶክ ክፍል ሌንጮ ለታ ፣ ዲማ ነገዎ፣ እንደክብር እንግዳ አበባ ሲረጭላቸው የኢትዮጰያ አንድነት ላይ እንደ ዋዛ ሲሳለቁበት እንደነበር የሚዘነጉት ጉዳይ ነው ብዬ አላምንም ።በአማራው ላይ የነበረው ጭፍጨፋ ሲያኪያሂዱ የነበሩትን እነ ሌንጮን ፣ እነ ስዬን ፣ እነ ዲማ ነገዎን እየተቀበሉ በመድረኮቻቸው ሲያስተናግዱ ፣ካፈሰሱት የንጽሃን ደም በራሳችው ስልጣን ነፃ ሲያደርጓቸው እንደነበረ የሚረሳ አደለም።ምን አልባት ይህ አልተደረገም መረጃ አቅርብ እባል እንደሆነም አላውቅም።ለመሆኑ በአማራ ላይ በተደረገው ጭፍጨፋ እነ ሌንጮ ወይም እነስዬ ፀፀታቸውን ወይም ስህተተኝነታቸውን ተጠይቀው ነበር? እነ ፀጋዬ ደብተራውስ የት እንዳሉ ተጠይቀው ነበር። እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ግለሰቦች ይህ ሁሉ ግፍ ሲሰራ ስልጣን ላይ እንደነበሩ የሚታወቅ ነው።ታዲያ ምን የሚያስደንቅ ጉዳይ ሆኖ ነው የትግራይ ህዝብ በጅምላ አይወቀስ ስላልኩኝ ሊወቅሱኝ የተነሱት? መልሱ ግልጽ ነው የድርጅት ጥቅም ያገኙ መስሎቸው ነው።የድርጅት ጥቅም የሚገኘው በርትቶ በመስራት እንጂ እየተሽለከለኩ አቋምን በመደበቅ በስም ማጥፋት ዘመቻ ላይ በመሰማራት አደለም። መልዕክቱን ሳይሆን መልዕክተኛውን ለማጥቃት የሚደረገው ጥረት መልዕክቱን አይቀይረውም ።እንዲያውም የአስተሳሰብ ትንሽነትን ያጎላል እንጂ።

ለተወደደችው ሀገራችን የማይበጅ አካሄድ በመሆኑና ዘረኝነትን በሌላ መንገድ ለመውለድ የሚደረገውን ትግል እስከመጨረሻው እቃወማለሁ ። ሌንጮ ለታ በደኖን ለመድገም ጥረት ቢደርጉ ያኔ እንደታገልኩት አሁንም መታገሌ አይቀርም ። ኢትዮጵያ ሃገራችን እንደነ መላኩ ተፈራ፣ እንደነ መንግስቱ ሃይለ ማርያም አይነት ለአንድነት ቆመናል የሚሉ ፋሽሽቶች ፣ እንደነ መለስ ፣ ሌንጮ ለታ አይነት ፣ ዘረኛ ፋሽሽቶች ያየች አገር ነች ። አሁን እንደገና የሚቀጥላው መንግስት በቂም ላይ የተመሰረተ ጅማሮ ይኑረው የሚሉትን በግልፅ በአደባባይ አቋማቸውን የተሳሳተና የሃገሪቱን ህልውና የሕዝቡን አንድነት ከፍተኛ አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑን ከመናገር አልቆጠብም።

ውድ አቶ ጌታቸው

በመስተጨረሻም መልዕክቴን ተረድተው ለሌሎች ለማስረዳት ያደረጉት ጥረት እያመሰገንኩ በአቋማችን ፀንተን ብሩህዋን ኢትዮጵያ ለመመስረት ትግላችንን እንድንቀጥል አደራ እያልኩ በግሌ በዚህ በማይረባ እንካ ሰላምቲያ ውስጥ ለመግባት ስላፈለግሁ በቀጥታ ለመመለስ ፍላጎት እንደሌለኝ እገልፅሎታለሁ። በሌላ በኩል ደግሞ ታላቅ የሆነ ስራ በመስራት ወያኔን የሚታገሉት መገናኛ ዘዴዎች እኔ ላስተላልፍ የፈለግሁትን መልዕክት ችላ

በማለት የማይጠቅም አተካራ ውስጥ በመግባት  ከእኔ ጋር ሙግት በመግጠም ግዜያቸውን እንዲያጠፉም ስለማልፈልግ ፅሁፌን በፅሞና አንብበው እንዲረዱኝ እጠይቃቸዋለሁ።

ስለኛ የሚስብ ሁሉ ሰላም ይክረም!!!!
አክባሪዎ በልጅግ አሊ